# ምዕራፍ አምስት
# ኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቲያኖች መድኃኒታችን ነው።

## 1. በብሉይ ኪዳን፤

የእግዚአብሔር ቃል መድኃኒት አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ሌላ መድኃኒት እንደሌለ ፍጡር እንደማያድን ይናገራል ለመረጃ የሚሆኑ ጥቅሶችን እንመልከት፦

"እኔ ግን ከግብጽ ምድር ጀምሬ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም ከእኔም በቀር ሌላ መድኃኒት የለም።" (ሆሴዕ 13÷4)

"እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኃኒትህ ነኝ።" (ኢሳ 43÷3) "እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም" (ኢሳ 43÷11) ተብሎ እንደተጻፈ ፍጡር ፍጡርን ሊያድነው ስላልቻለ እግዚአብሔር በመልክ የሚመስለውን በባሕርይ የሚተካከለውን መድኃኒት ለመላክ ተስፋ ሰጠ እርሱም (የሚመጣው) አምላክ ነውና መድኃኒት ተብሎ ተጠቀሰ። ስለሚመጣው መድኃኒት እንዲህ ተብሎ ተጻፈ።

"መድኃኒቴም አይዘገይም ከጽዮን ለክብር እንዲሆን መድኃኒትን ለእስራኤል ሰጥቻለሁ።" (ኢሣ 46÷13)

"ሰውም እንደሌለ አየ፣ ወደእርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት ጽድቁም አገዘው ጽድቅንም እንደጥሩር ለበሰ፣ በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቍር አደረገ የበቀልንም ልብስ ለበሰ በቅንዓትም መጎናጸፊያ ተጎናጸፈ እንደሥራቸው



መጠን እንዲሁ ቁጣን ለባለጋራዎቹ ፍዳንም ለጠላቶቹ ይከፍላል።" (ኢሳ 59÷16-18) "ዓይናችሁን ወደሰማይ አንሱ ወደታችም ወደምድር ተመልከቱ፡ ሰማያት እንደጢስ በንነው ይጠፋሉ እንደልብስ ታረጃለች፣ የሚኖሩባትም እንዲሁ ይሞታሉ ማዳኔ ግን ለዘለዓለም ይሆናል ጽድቄም አይፈርስም ጽድቄን የምታውቁ ሕጌም በልባችሁ ያለ ሕዝብ ሆይ ስሙኝ የሰውን ተግዳሮት አትፍሩ፣ በስድባቸውም አትደንግጡ እንደልብስም ብል ይበላቸዋል እንደ በግ ጠጕርም ትል ይበላቸዋል ጽድቄ ግን ለዘለዓለም ማዳኔም ለትውልድ ይሆናል።" (ኢሳ 51÷6-8) ተብሎ እንደተጻፈ ብሉይ ኪዳን አበክራ ይመጣል ያለችው የኛ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስን ነበር።

## 2. በሐዲስ ኪዳን፤

ሐዲስ ኪዳን ደግሞ ስለመድኃኒቱ መምጣት ብቻ ይናገራል ብንል ለእውነት የቀረበ ቅይጥ እውነት ሳይሆን ጥሩ እውነት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሳውያን ሰዎች ይመሠክራሉ፤ በብሉይ ኪዳን ያለ አንድ እግዚአብሔር መድኃኒት የለም መድኃኒት ይሆን ዘንድ ለፍጡር አይቻለውም ተብሎ የተጻፈው በሐዲስ ኪዳንም "መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" (ሐዋ 4÷12) ተብሎ ተተርጕሟል።

በዚህ ቃል አንደኛ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን ሁለተኛ ያለኢየሱስ ክርስቶስ መዳን የማይቻል መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። መልአኩ ገብርኤል "ልጅም ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ" (ማቴ 1÷21) በማለት በዮሴፍ በኩል ለዓለም መድኃኒትነቱን አወጀ። (ሉቃ 1÷31) እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም "ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች" (ሉቃ 1÷47) በማለት መድኃኒትነቱን መሠከረችልን፤ ዘካርያስም "የእስራኤል ጌታ

አምላክ ይባረክ ጎብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአልና ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደተናገረ በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነሥቶልናል ማዳኑም ከወደረኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው።" (ሉቃ 1፥68-72) አለን። ቅዱሳን መላእክትም "ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።" አረጋዊ ስምዖንም "ጌታ ሆይ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና።" (ሉቃ 2፥30-32) በማለት የእግዚአብሔርን ማዳን እንዳየ መሠከረ። ሳምራውያንም "እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን" (ዮሐ 4፥42) በማለት እምነታቸውን ገልጸዋል።

ባለቤቱም የመጣበትን ዓላማ "የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም" (ሉቃ 9፥56)

"የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና" (ሉቃ 19፥10) በማለት ገለጸልን። ሐዋርያትም በሁለተኛውና በታላቁ ሲኖዶሳቸው "ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን።" (የሐዋ 15፥11) በማለት እምነታቸውን ገለጹልን። እነቅዱስ ጳውሎስም "ወደ ውጭም አውጥቶ ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው እነርሱም በጌታ በኢየሱስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ" (የሐዋ 16፥30-31) ሲሉ ሰማናቸው። ቅዱሳን ሐዋርያትም በአይሁድ ሸንጎ "መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" (የሐዋ 4፥12) በማለት ሲያውጁ ቅ/ጳውሎስም "ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ።" (1ኛ ጢሞ 1፥15) በማለት ይመክረናል።



ክርስቲያን ወንድሜ፣ አባቴ እናቴ እህቴ ሆይ በዚህ ነገር በእርግጥ እናምናለንን? ኢየሱስ ክርስቶስ መተኪያ የሌለው መድኃኒት መሆኑን እንመን። ቅዱሳን ሐዋርያትም ከድካም እንድንድን ሌላ መድኃኒት ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ የለምና አትድከሙ ይሉናል። እኔም በበኩሌ ለክርስቲያኖች ሌላ መድኃኒት የለምና በእርሱ እንረፍ እላለሁ፤ እባካችሁ ባለመድኃኒቶች መስለዋችሁ ወደ ባለ ዛሮች ቃልቻዎች ቤት ወደጠንቋዮች ሰፈር በመባዘን ጊዜአችሁን አታጥፉ መድኃኒት አንድ እንደ ሆነ እመኑ በእርሱም ተደገፉ።

## ከምን አዳነን?

### ሀ. ከዘለዓለማዊ ሞት አድኖናል፤

በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ከዘለዓለማዊ ሞት ስለመዳናችን የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥክርነት እንመልከት።

"በዚህም ተራራ ላይ በወገኖች ሁሉ ላይ የተጣለውን መጋረጃ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋውን መሸፈኛ ያጠፋል። ሞትን ለዘለዓለም ይውጣል ጌታ እግዚአብሔር ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፤ የሕዝቡንም ስድብ ከምድር ሁሉ ላይ ያስወግዳል እግዚአብሔር ተናግሮአልና።" (ኢሳ 25፥6-7)

"ከሲኦል እጅ እታደጋቸዋለሁ ከሞትም እቤዣቸዋለሁ ሞት ሆይ ቸነፈርህ ወዴት አለ? ሲኦል ሆይ ማጥፋትህ ወዴት አለ? ርኅራኄ ከዓይኔ ተሰወረች።" (ሆሴዕ 13፥14) በማለት ልባችንን በጽኑዕ ተስፋ ሞላልን።

በሐዲስ ኪዳንም "አዎን ሙታንን በሚያነሣ በእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን እንዳንታመን እኛ ራሳችን የሞትን ፍርድ በውስጣችን ሰምተን ነበር እርሱም ይህን ከሚያህል ሞት አዳነን ያድነንማል፤ እናንተም ደግሞ ስለእኛ እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን በብዙ ሰዎች በኩል ስለተሰጠን ስለጸጋ ሥጦታ ብዙዎች ስለእኛ ያመሰግኑ ዘንድ ወደፊት ደግሞ እንዲያድነን በእርሱ ተስፋ አድርገናል።" (2ቆሮ 1፥9-11) ተብሎ ተጽፏል።

ክርስቲያን ወንድሜ ሆይ በኃጢአታችን ምክንያት ከሰለጠነብን ሞት፣ መሬት ጋር ከቀላቀለን ሞት፣ መታሰቢያችንን ለማጥፋት እጅ እግራችንን አሥሮ ወደመቃብር ካወረደን ሞት፣ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረ እኛነታችንን ለውጦ እንደ እንስሳት አዕምሮአችንን ንባባችንን አሳጥቶ እንደቅጠል ካረገፈው ወደመሬት ከወተፈው ሞት በነፍስ በሥጋችን ከሰለጠነ ሞት ያዳነን ጌታ መሆኑን እርሱም ለሚያምኑበት ትንሣኤና ሕይወት መሆኑን በእርግጥ ልብ ብለኸዋልን አሁን ልብ በለው ሕይወትህ እርሱ ነውና።

## ለ. *ከኃጢአት አድኖናል፤*

የሰው ዘር ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ለመረጃ ያህል ሙሴ "እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁል ጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ።" (ዘፍ 6፥5) አለ።

ዘማሪውም "ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል በሥራቸው ረከሱ ጎሰቆሉ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም የሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም



አንድም ስንኳ የለም ጉሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው በምላሳቸውም ሸነገሉ" ብሏል (መዝ.13፥1-4)

"በሬ የገዥውን አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ እስራኤል ግን አላወቀም ሕዝቤም አላስተዋለም ኃጢአተኛ ወገንና በደል የተሞላበት ሕዝብ የክፉዎች ዘር ርኩሰትን የምታደርጉ ልጆች ሆይ ወዮላችሁ እግዚአብሔርን ትተዋልና የእስራኤልንም ቅዱስ አቃልለዋል ወደ ኋላቸውም እየሄዱ ተለይተዋል ደግሞስ ዓመፃ እየጨመራችሁ ለምን ገና ትቀሠፋላችሁ? ራስ ሁሉ ለሕመም ልብ ሁሉ ለድካም ሆኖአል።" በማለት ኢሳይያስም ምሥክርነታቸውን አጸደቀ። (ኢሳ 1፥3-6)

ሰሎሞንም በበኩሉ "ልቤን አነጻሁ ከኃጢአትም ጠራሁ የሚል ማነው?" በማለት ይስማማል (ምሳሌ 20፥9)

ኢዮብም "ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ጻድቅስ ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድር ነው?" (ኢዮ 15፥14) በማለት ሐሳባቸውን ያጸድቃል፤ ለምን ብለን ብንጠይቅ ሐዋርያው "ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል።" (ገላ 3፥22) በማለት ያጠቃልላል ታዲያ ይህ ኃጢአተኛ የሰው ዘር እንዴት ሊድን ቻለ? ቢባል በወንጌል "ልጅም ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ" (ማቴ 1፥21) ተብሎ እንደተጻፈ ሐዋርያውም "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና" (ሮሜ 8፥1-2) ብሎ እንደተናገረ በመስቀሉ በሕማሙ በሞቱ በትንሣኤው አድኖናል።

በመስቀሉ ኃጢአታችንን ስለመሸከሙ "ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ

በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ" (1ጴጥ 2፥24) የተባለውን እንገንዘብ በሞቱም ከኃጢአት ስለመዳናችን "ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" (1ጴጥ 3፥18) "እንዲህ ቢሆንስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል" (ዕብ.9፥26) ተብሎ የተጻፈውን ማንበብ ማስተዋል ይገባል በሕማሙ፣ በስቅለቱ በሞቱ ከኃጢአታችን ላዳነን ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም ከፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ ጋር "ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ ለእርሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን" (ራእ 1፥6-7) በማለት ልንዘምርለት ይገባል።

### ሐ. ከዲያብሎስ ባርነት፤

ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን የላሜ ልጅ የአውራዬ ውላጅ በማለት ነጻነታችንን ገፎ በአርአያ እግዚአብሔር በአምሳለ እግዚአብሔር የተፈጠርነውን ለእንጨት ለድንጋይ በማንበርከክ በሞተ ሥጋ በሞተ ነፍስ አስጨንቆ አስጠብቦ ገዝቶን ነበር። ነገር ግን "እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ሥርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።" (ቆላ 1፥13) ተብሎ እንደተጻፈ ነጻ ወጥተናል።

ከዚህ ሌላ ከደዌ ከሕማም ከክፉው ዓለም ከዲያብሎስ አሠራር ነጻ አውጥቶናል።

## 3. ኢየሱስ አምላካችን ነው።

ይህን ንዑስ ርዕስ ኢየሱስ ማነው በሚለው ውስጥ በሠፊው ስላየነው በማስገንዘቢያ ጥቅሶች እናልፈዋለን ነገር ግን ጥቅሶችን በሥርዓት



በሚያገናዝብ አዕምሮ ብንመለከታቸው በጣሙኑ በእምነታችን ይጠብቁናል ጥቅሶቹም የሚከተሉት ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ዮሐ 1፥1-5 | ዮሐ 5፥18 | 1ቆሮ 8፥6 |
| የሐዋ 20፥28 | ዮሐ 10፥30-39 | ኤፌ 4፥5-6 |
| ዮሐ 20፥28 | ራዕ 1፥8, ኢሳ 44፥6 | ፊል 2፥5-6 |
| ሮሜ 5፥9 | ራዕ 1፥18 | ቆላ 1፥15-18 |
| 1ዮሐ 5፥20-21 | ኢሳ 48፥12-13፤ | 1ጢሞ 1፥17, 6፥14-16 |
| ኢሳ 9፥6-10 | ራዕ 21፥6, ራዕ 22፥13 | ቲቶ 2፥13 |
| | | ይሁዳ 4፥25 |

### 3.1 ፈጣሪ ነው

ዘፍ 1፥1, ዮሐ 1፥1-3
ዘፀ 2፥7, 1ቆሮ 8፥6
ኢሳ 45፥11-18,
ኤፌ 3፥9 ሚል 2፥10
ቆላ 1፥12-17
ኢሳ 40፥28, ዕብ 1፥12

### 3.2 ያለና የሚኖር አምላክ ነው

ዘዳ 3፥13-14 ራዕ 1፥7-8
ኢሳ 43፥10 ዮሐ 18፥5-8
ዮሐ 8፥24-28

### 3.3 መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው አምላክ ነው

ኢሳ 41፥4, ራዕ 1፥17
ኢሳ 43፥10-11, ራዕ 21፥6
ኢሳ 44፥6-8, ራዕ 22፥13

በነዚህና በሌሎችም የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች እንደምናነበው ፈጣሪ ነውና እንታመነው፣ አምላክ ነውና እንገዛለት፣ ያለና የነበረ በባሕርዩ ሞት በመንግሥቱ ሽረት የሌለበት አምላክ ነውና እናምልከው።

## 3.4 ለዘለዓለም የነገሠ ንጉሥ የሆነ አምላክ ነው።

"እናንተ መኳንንቶች በሮችን ክፈቱ የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ የክብርም ንጉሥ ይግባ ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው ብርቱና ኃያል እግዚአብሔር ነው በሰልፍ ኃያል፣ እናንተ መኳንንቶች በሮችን ክፈቱ፣ የዘለዓለም ደጆች ይከፈቱ፣ የክብርም ንጉሥይግባ፤ ይህ የክብር ንጉሥ ማነው? የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር እርሱ የክብር ንጉሥ ነው።" (መዝ 23፥7-10) በማለት ዳዊት የተናገረውን "ኢየሱስም በይሁዳ ቤተልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ እነሆ ሰብአሰገል የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ ንጉሡ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ፤ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው። እነርሱም፦ አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገዥዎች ከቶ አታንሺም ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተልሔም ነው አሉት" (ማቴ 2፥1-6) በማለት ሐዲስ ኪዳን ለኢየሱስ ሰጥቶ መናገሩ "እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው በምድርም መካከል መድኃኒት አደረገ" (መዝ 73፥12) ዘማሪው ያለውን ጲላጦስም "እንግዲያ ንጉሥ ነህን አለው ኢየሱስም መልሶ እኔ ንጉሥ እንደሆንሁ አንተ ትላለህ" (ዮሐ 18፥37) በማለት ጌታችን መናገሩ ኤርምያስም "እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው እርሱም ሕያው አምላክና የዘለዓለም ንጉሥ ነው ከቁጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች አሕዛብም መዓቱን አይችሉም።" (ኤር 10፥10) በማለት በመሠከረበት በዚያው መንፈስ ዮሐንስ በራዕዩ "ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው ጌታ ሆይ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ



ቅዱስ ነህና የጽድቅም ሥራህ ስለተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ።" (ራእይ 15፥3-4) በማለት ሲዘምሩ የሰማውን መሥክሯል። ዘካርያስም አስቀድሞ "እግዚአብሔርም በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል በዚያ ቀን እግዚአብሔር አንድ ስሙም አንድ ይሆናል።" (ዘካ 14፥9) በማለት መመሥከሩ ዮሐንስም ዘካርያስ በተነበየበት በዚያው መንፈስ "በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው።" (ራእይ 19፥16) ብሎ መተርጎሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ ንጉሥ በመሆኑ አይደለምን? ክርስቲያኖች የነፍሳችን መድኃኒትና ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ይህም መንግሥቱ መለኮታዊ መሆኑን ልብ እንበል፤ ለእርሱም እንገዛ ከእርሱም ጋር እንኑር ከላይ የጠቀስነው ዳዊት በመዝ 23፥7-10 የመከረንን በማስተዋል ለንጉሡ የልባችንን በሮች እንክፈት ከእርሱ ጋር አብረን ለመኖር ፈቃደኞች እንሁን።

"እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።" (ራዕይ 3፥20) በማለት እንደነገረን በርኅራኄ የተሞላው ንጉሥ በበራችን ቆሞአልና እንክፈትለት ይግባ አብረንም ከእርሱ ጋር ለመኖር እግዚአብሔር ይፍቀድ አሜን።

## 4. ኢየሱስ ክርስቶስ እረኛችን ነው፤

"መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል ተኩላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል። ሞያተኛ ስለሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል መልካም እረኛ እኔ ነኝ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን

እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል ነፍሴንም ስለበጎች አኖራለሁ።" (ዮሐ 10፤11-15) እንዳለ ጌታችን እረኛ ለቤተክርስቲያን እርሱ ነው እንደቅጥረኛ እረኛ በጎቹን በማሰማራት ፈንታ ወደ እረፍት መስክ (መዝ 22፤1-2) እራሱን ያላሰማራ፣ በአደራና በጠባቂነት የተሰጧቸውን በጎች እያረዱ እየበሉ አውሬ በላቸው እንደሚሉ ቅጥረኞች ያይደለ እረኛ በጎቹ እስከሚበርዳቸው ድረስ ያለ አግባብ ጠጉራቸውን እንደሚሸልቱ ቅጥረኞች ያልሆነ፣ ታማሚ በጎችን እንዳላከሙ፣ ደካማዎችን እንዳላዳኑ ሰባራዎቹን እንዳልጠገኑ፣ የጠፉትን በጎች ወደ መንጋው በመመለስ ፈንታ ወሬያቸውን በመሰለቅ ከወንበራቸው ተቀምጠው እንዳልሰበሰቡ እረኞች ያይደለ የጠፉትን የሚሰበስብ እረኛ ነው።

የሰቡትና የወፈሩት አንዳንድ በጎች ምስኪኖችን የከሱትን በጎች እየገፉ ከበረት ሲያስወጧቸው በቀንዳቸው ሲወጓቸው ሲያቆስሏቸው ሲያደሟቸው የሚጠጡትን ውኃ ሲያደፈርሱባቸው ምግባቸውን ሲረግጡባቸው እያዩ ከመቀመጫቸው ላለመነሣት ገዝም ብለው እንደሚያዩ ቅጥረኞች ያይደለ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ እረኛችን ነውና "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝም የለም በለመለመ መስክ ያሳድረኛል" (መዝ 22፤1-2) ተብሎ እንደተጻፈ ወደለመለመ መስክ ወደ ወንጌል ወደ እረፍተ መንግሥተ ሰማያት ይመራናልና ኢየሱስ እረኛችን ነው። "ይህንም ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ ሲል መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ ዘጠና ዘጠኙን በበረኃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል ወደ ቤትም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጐረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል እላችኋለሁ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ



በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።" (ሉቃ 15፥3-7) ተብሎ እንደተጻፈ ከባዘንበት ምድረ በዳ ከጠፋንበት ውድማ ይፈልገናል ያገኘናል በደረቱ ይታቀፈናል በትከሻው ይሸከመናል ወደመንጋው ይሰበስበናል ይቀላቅለናል፤ ዳዊት በእረኝነቱ ለበጎቹ ሲል እንዴት ከአራዊት ጋር እንደታገለ በጎቹንም በምን ዓይነት መንገድ ከአራዊት መንጋጋ እንዳስጣለ "ዳዊትም ሳኦልን አለው፦ እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሣና ድብ ይመጣ ነበር። ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር፤ በኋላም እከተለውና እመታው ነበር፤ ከአፉም አስጥለው ነበር፤ በተነሣብኝም ጊዜ ጉሮሮውን ይገፍ እመታውና እገድለው ነበር" (1ሳሙ 17፥34-35) የተባለውን እንገንዘብ ዳዊት በጎቹን ታግሎ እንዳዳነ እኛንም እረኛችን ኢየሱስ ከዲያብሎስ ጉሮሮ ከአንበሳ መንጋጋ አድኖናል ወደፊትም ይጠብቀናል።

## የእረኛውና የበጎቹ ግዴታዎች

### 1. የበጎቹ ግዴታዎች፤

#### 1.1 በረኛው በሩን ሊከፍትለት ይገባል፦ (ዮሐ 10፥2)

በረኛው የእኛ የኅሊና ፈቃድ ነው የእግዚአብሔር ቃል "እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል" (ራእይ 3፥20) "እናንተ መኳንንቶች በሮችን ክፈቱ የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ የክብርም ንጉሥ ይግባ ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው? እግዚአብሔር ነው ብርቱና ኃያል እግዚአብሔር ነው በሰልፍ ኃያል፣ እናንተ መኳንንቶች በሮችን ክፈቱ፣ የዘለዓለም ደጆች ይከፈቱ፣ የክብርም ንጉሥ ይግባ፤ ይህ የክብር ንጉሥ ማንነው? የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር እርሱ የክብር ንጉሥ ነው።" (መዝ 23፥7-10) ይላል እረኛው በሩ ተከፍቶለት ይሆንን? በእያንዳንዳችን ሕይወት እውነተኛው እረኛ

በበሩ ካልሆነ እንደሌላው እንደወንበዴው አጥር ጥሶ ግንብ አፍርሶ አይገባምና ስሩን እንከፍትለት ዘንድ ይገባል።

## 1.2 ድምፁን መስማት አለባቸው (የበጎች ግዴታ) (ዮሐ.10፥1-15)

የእግዚአብሔር ቃል "እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘለዓለም ሞትን አያይም።" (ዮሐ 8፥51)

"ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል እናንተ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና ስለዚህ አትሰሙም።" (ዮሐ 8፥47)

"ጲላጦስም እንግዲያ ንጉሥ ነህን አለው ኢየሱስም መልሶ፡- እኔ ንጉሥ እንደሆንሁ አንተ ትላለህ እኔ ለእውነት ልመሠክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደዓለም መጥቻለሁ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው።" (ዮሐ 18፥37)

"ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል ዝናብም ወረደ ጐርፋም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው ወደቀም አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።" (ማቴ 7፥24-25) በማለት ጌታ የተናገረውን ልንሰማ ይገባል፤ ማንም ከእረኛው ከኢየሱስ ወንጌል የሚርቅ በግ ሳይሆን የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ ነው።

## 1.3 የእረኛቸውን ድምጽ በሚገባ መለየት አለባቸው፤

"የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል ከሌላው ግን ይሸሹታል እንጂ አይከተሉትም የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና።" (ዮሐ 10፥4-5) ተብሎ



እንደተነገረ የእውነተኛው እረኛ ድምፅ ከሌላው ድምፅ ሰው ሠራሹን ወንጌል ከመለኮታዊው ወንጌል ፍጡራንን ከፈጣሪ ለይቶ ማወቅ እውነተኛውንም እረኛ መከተል ያሻቸዋል።

## 1.4 በሩ እርሱ መሆኑን ሊያውቁ ይገባል፤

"ኢየሱስም ደግሞ አላቸው እውነት እውነት እላችኋለሁ እኔ የበጎች በር ነኝ።" (ዮሐ 10፥7)

"በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።" (ዮሐ 10፥9) ተብሎ እንደተነገረን በጎች በሰላም ወጥተው በሰላም ለመግባት ወደእረፍት ውሃ ለመሠማራት በለመለመ መስክ ቆይቶ ወደበረት ለመግባት በሩ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ማወቅ ይገባቸዋል። በጎቹ እነዚህንና የመሳሰሉትን ካሟሉ በሕይወት ይኖራሉ።

# 2. የእረኛው ግዴታዎች፤

## 2.1 በጎቹን በስማቸው ማወቅ፤

"የራሱን በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል" (ዮሐ 10፥3) አዎን ኢየሱስ ክርስቶስ በስማችን ያውቀናል (ዮሐ 20፥16, ማር 3፥16-19)

## 2.2 ከፊት ሆኖ መምራት፤

"የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል።" (ዮሐ 10፥4) የእኛ እረኛ በኋላ ሆኖ አራዊት ወዳሉበት በጎችን በግድየለሽነት እየደበደበ የሚወስድ (የሚነዳ) ሳይሆን በጎቹ የሚያዘግሙት አዝግመው የሚፈጥኑትም ፈጥነው እንዲደርሱ በነጻነት እንዲጓዙ በፊት በፊታቸው ክፉ እንዳያገኛቸው አውሬ እንዳያስደነግጣቸው ፊጥኖ ፊት ፊት በመሄድ ክፉውን የሚጋፈጥላቸው መልካም ዕረኛ ነው። የእግዚአብሔር ቃልም

እንድንከተለው “እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምሥክሮች እንደደመና በዙሪያችን ካሉልን እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትሥግስት እንሩጥ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሶ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።” ይለናል (ዕብ 12፥1-2) መልካም እረኛ ነውና እንከተለው።

## 2.3 ነፍሱን ስለበጎቹ ማኖር፤

“መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል” (ዮሐ 10፥11) ተብሎ እንደተጻፈ ስለበጎቹ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ እረኛ ነው።

## 2.4 የባዘኑትን በጎች መመለስ፤

“ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ አንድም መንጋ ይሆናሉ።” (ዮሐ 10፥16) ተብሎ እንደተጻፈ የባዘኑትን በጎች አንድ ያደርጋል።

## በተጨማሪ ሊጤኑ የሚገባቸው ነገሮች

1. የእኛ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ለመሆኑ ከምንገነዘባቸው ነጥቦች አንዱ ይህ እረኛ የሚለው ነጥብ ነው። በብሉይ ኪዳን ስለእግዚአብሔር እረኝነት የተነገረው ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ሰለ ኢየሱስ ክርስቶስ መነገሩ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል (መዝ. 22፥1, ሕዝ 34፥11-24,) የተነገረውን ከዮሐ 10፥14-15 ዕብ 13፥20, 1ጴጥ 2፥25 ጋር በማገናዘብ ይመልከቱና የእረኛዎን መለኮታዊነት ይገንዘቡ።



2. ረብ (ሥጋዊ ጥቅም) ለማግኘት ባለማቀድ በግድ ሣይሆን በፍቅር በማስተዳደር ለመንጋው ምሣሌ በመሆን መንጋውን የሚጠብቁ እረኞችን ሾሞአልና እነርሱን ይስሙ፤ ሕገ ተሰብኦን (የሰውን ሕግ) ፈጽሞ ማረጉን ልብ ይበሉ ጥቅሶቹም 1ጴጥ 2፥25, ዮሐ 21፥15-18, ኤፌ 4፥11, 1ጴጥ 6፥1-4

እርስዎም የእረኛዎችዎንም ድምጽ ይስሙ ለእነርሱም ይታዘዙ “የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው” (ዕብ.13፥7) ተብሎ ተጽፎአልና።

## 5. ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላማችን ነው።

የዓለም ቤዛ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ተብሎ ይጠራል “ሕጻን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ፣ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።” (ኢሳ 9፥6-7) ተብሎ እንደተተነበየ የሰላም አለቃ ነው ሐዋርያውም “የሰላም አምላክ ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን” (ሮሜ 15፥33) እንዲሁም “የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል።” (ሮሜ 16፥20) ብሎ እንደመሠከረ የሰላም አምላክ መሆኑንም እንገንዘብ።

የሰላም አለቃ፣ የሰላም ንጉሥ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ የተዘመረው መዝሙር በሰማያውያን ቅዱሳን መላእክትም ሆነ በምድራውያን እረኞች ዘንድ “ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ።” (ሉቃ 2፥13-14) የሚል ነበር። በእርሱ አምነን ከሁከት እንድንድን “ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ” በማለት ተናግሮአል (ዮሐ 14፥1) እርሱ የሚሰጠንም የሰላም ዓ

ይነት ከዓለማችን ሰላም የተለየ ሰላም መሆኑን "ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም ልባችሁ አይታወክ አይፍራም» በማለት ነግሮናል (ዮሐ 14÷27) ደቀመዛሙርቱንም ለወንጌል አስተምህሮ ሲልካቸው "ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር ሰላማችሁ ያድርበታል አለዚያም ይመለስላችኋል።" (ሉቃ 10÷56) ነበር ያላቸው። እርሱም ራሱ ከሙታን ተነሥቶ ሰላማቸው በተወሰደባቸው ቤታቸውን ዘግተው በተቀመጡት ደቀመዛሙርት መካከል በዝግ ቤት ውስጥ ገብቶ "በመካከላቸውም ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይሁን" ነበር ያላቸው (ዮሐ 20÷19)

አዎን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል "እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና" (ቆላ 1፤20) ተብሎ እንደተጻፈ የዚህ ዓለም ገዥ ዲያብሎስ የማያደፈርሰው ሰላም ተሰጥቶናል ያም ሰላም "አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።" (ፊልጵ 4፤7) እንደተባለ አእምሮን የሚያልፍ ሰላም ነው ያም ሰላም ልቦናችንን ሊገዛ እንደሚገባው መጽሐፍ ቅዱስ "በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይብዛ የምታመሰግኑም ሁኑ" ይለናል (ቆላ 3፤15) በዚህ ሰላምም እንኖርበት ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል "ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ" (ሮሜ 12÷8) "በሰላም ሁኑ" ይለናል። (1ተሰ 5፤13-14)።

ክርስቲያኖች ሆይ የመንፈስ ፍሬ የሆነውን ሰላምን (ገላ 5፤22) እንዴት መያገ እንደምንችል ሕያው ቃሉ "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያገ" በማለት ይመክረናል። (ሮሜ 5÷1) "አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ



የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምን ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው።" (ኤፌ 2÷13-16) እንዳለ ሐዋርያው የክርስቲያኖች ሰላም የጥልን ግድግዳ በመስቀሉ ያፈራረሰ ጌታ ጥልን የገደለ የተለያዩትን ያዋሐደ ሕያው ንጉሥ ነውና።

አንባቢ ሆይ የአንተስ ሰላም ማን ነው? ለመሆኑ ሰላም አለህን ሰላም ከሌለህ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን ያዝ፣ እርሱ ሰላምህ ነውና "ኦ ንጉሠ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ ስላመከ ኃበነ - የሰላም ንጉሥ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሰላምህን ስጠን አሜን"

## 6. ኢየሱስ ክርስቶስ ምሣሌያችን ነው።

### 6.1 ልባችንን ትሁት እናደርግ ዘንድ፤

እኛም ስለጽድቅ የዋኃን እንሆን ዘንድ ምሳሌያችን ነው "ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደእኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።" ብሏል (ማቴ 11÷28-30) አንባቢ ሆይ አንተስ ጌታህን ትመስለው ዘንድ ትሁት ልብ አለህን? እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጃትን ምድር ትወርስ ዘንድ ስለጽድቅ የዋህ ነህን? (ማቴ 5÷5)

### 6.2 ለትኅትናና ለአገልግሎት ራስን ዝቅ ለማድረግ ምሣሌያችን ነው።

"እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንሥቶ ዳግመኛ ተቀመጠ እንዲህም አላቸው ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ መምህር ጌታ ትሉኛላችሁ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሣሌ ሰጥቻችኋለሁና፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም።" (ዮሐ.13፥12-16) ይላል የእኛ ጌታ ምሳሌውን ተቀብለሃልን ከአንተ በታች የሆኑትን ለማገልገል ፈቃደኛ ነህን?

### 6.3 በክፉው ዓለም ለመጠላታችን ምሣሌያችን ነው።

"ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እወቁ ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር ነገር ግን እኔ ከዓ ለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለአይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል ባሪያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኳችሁን ቃል አስቡ እኔን አሳደውኝ እንደሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ይህን ሁሉ ስለስሜ ያደርጉባችኋል።" (ዮሐ 15፥18-21)

አንባቢ ክርስቲያን ሆይ ዓለም ስላልተቀበለህ ስለስሙ ስለተናቅህ ቅር ብሎህ ነበረን ምሳሌህ ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከት እርሱን እንኳ ክፉው ዓለም አልወደደውም አንተም ከዓለም ካልሆንክ ዓለም ይጠላህ ዘንድ ግድ ነው ባሪያ ከጌታው አይበልጥምና አይዞህ በርታ።

### 6.4 በግፍ ለምንቀበለው መከራ ምሳሌያችን ነው።

"በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኀዘንን ቢታገሥ ምሥጋና ይገባዋልና። ኃጢአትን አድርጋችሁ ስትጎሠሙ ብትታገሡ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን



ስትቀበሉ ብትታገሡ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምሥጋና ይገባዋል፤ የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሣሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀብሎአልና እርሱም ኃጢአት አላደረገም ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ።" (1ጴጥ 2፥19-23) ይላል ቅ/ጴጥሮስ አባታችን።

አንባቢ ክርስቲያን ሆይ መልካም አድርገህ በተነሰምክ ጊዜ እስቲ አሁን ምን አደረግሁ እንዲሁ የሚያሰቃዩኝ ከእኔና ከአሳዳጆቼ ማን ተሽሎ ነው ብለህ የአሳዳጆችህን ሥጋዊነት ከአንተ መንፈሳዊነት ጋር አነጻጽረህ አዝነህ ታውቃለህን? አይዞህ በርታ ምሳሌህን ኢየሱስንም ተመልከት እርሱ እውነት ሲሆን የሐሰት ሰዎች ወንጅለውታልና ጻድቀ ባሕርይ ሲሆን ኃጢአተኞች ኮንነውታልና አትደነቅ።

### 6.5 ከእኛ ጥቅምና ክብር ይልቅ ለወንድሞቻችን ጥቅምና ክብር እንቆም ዘንድ እርሱ ምሳሌያችን ነው፤

"ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራውን ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም ነገር ግን የባሪያን መልክ ይ// በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ በምስሉም እንደሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።" (ፊልጵ 2፥3-8)

እንባቢ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ራሱን ዝቅ አድርጐ መዋቲ ሥጋን ለብሶ እንደመጣ ስለሰዎች መዳን ሌሎችንም ስለማክበር ራስህን ዝቅ ብታደርግ ኢየሱስ ክርስቶስን ትመስለዋለህ። በተጨማሪ ሮሜ 8፥29, 1ዮሐ 2፥6 1ቆሮ 11፥1 ይመልከቱ።

## 6.6 እኛ ክርስቲያኖች ለሌሎች ምሳሌዎች መሆን እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ያዘናል፤

### 6.6.1 በክርስቲያናዊና በመልካም ሥራችን ለሌሎች ምሳሌ እንሁን፤

"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።" (ማቴ 5፥14-16)

አንተስ ብርሃንህን በሰዎች ፊት የምታበራ ነህን? ወይስ ለአንተም ጨልሞብሃል? ሐዋርያውም "በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታንጎራጉሩ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ ስለዚህም በከንቱ እንዳልሮጥሁ በከንቱም እንዳልደከምሁ በክርስቶስ ቀን የምመካበት ይሆንልኛል።" (ፊልጵ 2፥14-15) ይላል። አንተም ዘይት ያልሞሉትን ሰነፎች ይመስል በሩ እንዳይዘጋብህ ዘይትህን ይህን ጊዜ ሙላና ለአንተም ሆነ ለጠማማው ትውልድ በመልካም ሥራ ምሳሌ ሁን (ማቴ 25፥1-10)



### 6.6.2 ለሚያምኑት ሁሉ በቃል፣ በኑሮ፣ በፍቅር፣ በእምነት፣ በንጽሕና ምሳሌ እንሁን፤

"ይህን እዘዝና አስተምር፤ በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑት ሁሉ ምሳሌ ሁን እንጂ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው እስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።" (1ጢሞ 4፥11-13) በማለት ልጁን ጢሞቴዎስን ቅዱስ አባታችን ጳውሎስ የመከረበት መንፈሳዊ ምክር ዛሬም እያንዳንዳችንን እንደሚመለከት አንዘንጋ።

### 6.6.3 የእኛ ተቃዋሚዎች ስለእኛ የሚናገሩትን እስኪያጡ ድረስ ራሳችንን በመግዛት ምሳሌዎች እንሁን፤

"የሚቃወም ሰው ስለእኛ የሚናገረውን መጥፎ ነገር ሲያጣ እንዲያፍር በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግህ ምሳሌ የሚሆን ራስህን አሳይ በትምህርትህም ደኅንነትን፣ ጭምትነትን ጤናማና የማይነቀፍ ንግግርን ግለጥ።" (ቲቶ 2፥7-8) ይላል የእግዚአብሔር ቃል።

ክርስቲያን ወገኔ ሆይ ከሳሽህን እስክታሣፍር ድረስ በቅድስና አርአያና ለሌሎችም ምሳሌ ሁነሃል? ወይስ በታማህበት ተገኝተሃል? በተጨማሪ ቅዱስ አባትህ ቅ/ጴጥሮስ "ስለሚመለከቱት ስለመልካም ሥራችሁ ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር በሚጎበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።" (1ጴጥ 2፥12) በማለት ለሁላችን የመከረውን ሕያው ምክሩን ሰምተህ ከሆነ ኑሮህ መልካም ለሌሎች ምሳሌ ይሁን እርሱን መስለን ሌሎችን በምሳሌነት ለመጥቀም እንዘጋጅ እግዚአብሔርም ይርዳን፤ አሜን!

## 6.7 ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታችን ነው፤

የሰው ልጅ በኃጢአቱ እንዳይሞት "ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።" (ዘፍ 2÷17) ብሎ ፈጣሪው የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ባለመቀበሉ "ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህ" (ዘፍ 3÷19) ተብሎ ተረገመ፤ ዘማሪው "በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ በታችኛው ጉድጓድ አስቀመጥኸኝ፤ በእኔ ላይ ቁጣህ ጸና መቅሠፍትህን ሁሉ በእኔ ላይ አመጣህ።" (መዝ 87÷6-7) በማለት እንደተናገረው በሞት ጥላ ሲኖር ሳለ "መዓትህንም ሁሉ አስወገድህ ከቁጣህ መቅሠፍት ተመለስህ መድኃኒታችን አምላክ ሆይ መልሰን ቁጣህንም ከእኛ መልስ በውኑ ለዘለዓለም ትቆጣናለህን? ቁጣህንስ ለልጅ ልጅ ታስረዝማለህን?" (መዝ 84፤3-5) ብሎ በምሬት ያለቀሰውን ልቅሶውን ሰምቶ ልጁ በሞት ጥላ በክህደት ጨለማ ለነበረው ሕዝብ "በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ በሞት ጥላ አገር ለሚኖሩም ብርሃን ወጣላቸው" (ኢሳ 9፤2) ተብሎ እንደተጻፈ ከመሰናክል የሚያድን ብርሃን (ዮሐ 3፤18-26) ከሞት ከመቃብር የሚያወጣ ትንሣኤና ሕይወት (ዮሐ 11፤25) ሆኖ መጣ እርሱም "እኔ መንገድ እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደአብ የሚመጣ የለም" (ዮሐ 14፤6) "እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚጠብቅ ለዘለዓ ለም ሞትን አያይም" (ዮሐ 8፤51) በማለት አበሠረን።፡

### 6.7.1 የሞት ጥላ የክሕደት ጨለማ በእርሱ ተወገደ፤

ነቢዩ ኢሳይያስ ከብዙ ዘመናት በፊት "በዚህም ተራራ ላይ በወገኖች ሁሉ ላይ የተጣለውን መጋረጃ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋውን መሸፈኛ ያጠፋል ሞትን ለዘለዓለም ይውጣል ጌታ እግዚአብሔርም ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል የሕዝቡንም ስድብ ከምድር



ሁሉ ያስወግዳል እግዚአብሔር ተናግሮአልና።" (ኢሳ 25÷7-8) ብሎ ተናግሮ ነበር። መልአከ ሞት ዲያብሎስን ከሥልጣኑ በመሻር (ዕብ 2÷14-15) የሞትና የሲኦልን መክፈቻ በመቀማት፣ የዲያብሎስን ሦስቱን ሥራዎች ማለትም ሞትን (ዮሐ 8÷44), ሐሰትን (8÷44), ኃጢአትን (1ዮሐ 3÷7-8) በማፍረስ በመስቀሉ የጥልን ግድግዳ በመናድ (ኤፌ2÷13-16) የሞትን መጋረጃ በመቅደድ እኛን በብርሃን ዙፋን አስቀመጠን።

### 6.7.2 ባለቤቱ እርሱ ራሱ ሕይወት ሊሆነን መምጣቱን ገለጸልን፤

ከዚህ የሚከተሉትን ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመልከት (ዮሐ 5÷21, 10÷10, 11÷25, 14÷6, 17÷3) በእርግጥ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓ ለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደዓለም አልላከውምና።" (ዮሐ3÷16-17) ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታችን ነው።

### 6.7.3 አባቶቻችን ሐዋርያት ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ ነው አሉ፤

ሐዋርያው ዮሐንስ "በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።" (ዮሐ 3÷36) "ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።" ይለናል (1ዮሐ 5÷12)

ቅዱስ ጳውሎስም "አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል፤ ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና፤ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ

ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል ክርስቶስ እንደበኩራት ነው በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው።" (1ቆሮ 15፥20-24)

"እንዲሁ ደግሞ ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ" (1ቆሮ 15፥45) አለ። በሮሜ መልእክቱም "በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፣ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ሥጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።" (ሮሜ 5፥17)

"ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፣ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።" (ሮሜ 8፥11) ይለናል። በኤፌሶን መልእክቱም "ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፣ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን።" (ኤፌ.2፥1-5) ይለናል፤ በቈላስይስ መልእክቱም "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም ሞታችኋልና፣ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ።" (ቈላ 3፥1-4) በማለት ሕይወታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲሰብክልን እንሰማዋለን። በዕብራውያን መልእክቱም "እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው፣ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሠሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።" (ዕብ 2፥14-15) በማለት በሕይወታችን ዘመን ሞትን በመፍራት ለምንኖረው ሁሉ ነጻነትን እንደሰጠን ይናገራል።



አንባቢ ሆይ ለአንተ ሕይወትህ ማን ይመስልሃል? በማንስ ላይ ተስፋ አድርገሃል? በኢየሱስ ክርስቶስ ነውን? አምላክህ የሚልህን ስማው እኔ ሕይወትህ ነኝ ይልሃል፤ ሐዋርያትም ኢየሱስ ነው ይሉሃል አዎን የሰው ልጆች ሁሉ ሕይወት እርሱ ነው በእርሱ የሚያምን ሁሉ ሕያው ነው።

## 6.8 ኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቲያኖች ድል አድራጊ መሪያችን ነው።

የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰሎሞን ይልቅ የሰዎችን የልብ እንቆቅልሽ የሚፈታ (ማቴ 12፥24) ከዮናስ ይልቅ የሰዎችን ልብ በትምህርቱ የሚገዛ፣ ኃይላትን የሚያሳፍር አሸናፊዎችን ድል የሚነሣ የአሸናፊዎች አሸናፊ ኃይልን የሚሰጥ የኃይል ጌታ ሁሉን የሚያንበረክክ ዘለዓለማዊ ንጉሥ ነው በመሆኑም ሦስቱን አሸናፊዎቻችንን ጠላቶቻችንን ድል ነሥቶ ለእኛም ድልን አቀዳጅቶናል።

### ሦስቱ ጠላቶቻችን

### 6.8.1 ዲያብሎስን ጌታችን ድል ነሣልን፤

እንደ መብረቅ ከሰማይ ወደምድር በስሙ በሰብአው አርድዕት ፊት ጣለው "ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው፡- ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደመብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።" (ሉቃ 10፥17-18) አላቸው ስሙም ሲጠራ ድል የነሣላቸው ስለስሙ እርሱ ነበርና።

### 6.8.2 ጠላታችን ዲያብሎስን ወደውጭ ጣለው፤

"አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል።" (ዮሐ 12፥31) "ስለፍርድም የዚህ ዓለም ገዥ

ስለተፈረደበት ነው።" (ዮሐ 16፥11) ከመንግሥተ ሰማያት በአፍአ ወደምትገኝ ወደገሃነም ጣለው ከሰዎች ልቡና አስወጣው በምድረ በዳ አቅበዘበዘው ማረፊያ ነሣው (ማቴ 12፥43-45) "ወገብረ ኃይለ በመዝራዕቱ ወዘረዎሙ ለእለ የዐብዩ ኀሊና ልቦሙ ወነሠቶሙ ለኃያላን እመናብርቲሆሙ" ማለት "በክንዱ (በወልድ) ኃይልን አደረገ ልቦናቸውን ከፍ ከፍ ያደረጉ አጋንንትን በተናቸው ኃያላን አጋንንትንም ከዙፋናቸው ከሰው ልቡና አስወጥቶ ሰደዳቸው" ብላ የመድኃኒታችን እናት እመቤታችን እንደዘመረችልን (ሉቃ 1፥51-53)

## 6.8.3 ጠላታችንን ከሥልጣኑ በመሻር ቁልፉን ቀማው፤

ስለሞት ፍርሃት በባርነት ያሠረንን ድል ነሣልን "እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሠሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ" በማለት በዕብራውያን እንደተናገረው (ዕብ 2፥14-15, ራዕ 1፥18)

## 6.8.4 ዓለምን (ክፉትን) ድል ነሣልን፤

ክፉው ዓለምም ጌታችንንም ሆነ እኛን ተከታዮቹን እንደማይወድ "ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እወቁ፤ ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለአይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል፤ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ እኔን አሳደውኝ እንደሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል ቃሌን ጠብቀው እንደሆነ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ።" (ዮሐ 15፥18-20) ተብሎ ተጽፎአል። የዓለምን ብርሃን ጌታችንን የማይወደው ለምንድነው ብለን ብንጠይቅ "ብርሃን



ወደ ዓለም ስለመጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራውን በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።" የሚል መልስ እናገኛለን (ዮሐ 3፥19-21) በመሆኑም ክፉው ዓለም የእኛም ሆነ የብርሃን ጠላት ነው። ይህን ጠላት ጌታችን ድል እንደነሣው "ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።" (ዮሐ 16፥33) ይለናል አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ።

ድል የነሣው ዓለም ምን ይመስል ነበር ብንል ሐዋርያው "ከእግዚአብሔር እንደሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን" (1ዮሐ 5፥19) ብሎ የሚያውቀውን ይመሰክርልናል እንዴት አድርጎ ድል ነሣው ብለን ብንጠይቅ ደግሞ "ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደአምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለኃጢአታችን ራሱን ሰጠ።" በማለት ሐዋርያው ይመልስልናል። (ገላ 1፥4)

## 6.8.5 በኃጢአት ያደፈውን የሥጋ ባሕርይ ድል ነሣልን፤

የሰው ልጅ ከኃጢአተኛ የሥጋ ባሕርይ የተነሣ ለሕግ መገዛት አልሆንለት ብሎ ይኖር እንደነበር ተጽፏል (ሮሜ 8፥3) የሰው ልጅ ሰውነትም የጦር ሜዳ መሆኑንና ሰውንም በውስጡ ያለው ሕግ ማርኮት እንደነበር በሐዋርያው "ሐዋዝ ውእቱ ሕገ እግዚአብሔር ዘውስተ ልብየ ወባሕቱ እረክብ ካልአ ሕገ ኃጢአት ውስተ አባልየ ወዔወወኒ መንገሌሁ ትሑት ብእሲ አነ መኑ እምአድኃነኒ እምዝንቱ ነፍስትየ መዋቲ" በአማርኛ ደግሞ "በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰውነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" (ሮሜ 7፥22-24)

ተብሎ እንደተጻፈ እንገነዘባለን ታዲያ ይህን ያህል ያስጨነቀንን ሕገ ሥጋ ድል የነሣልን ኢየሱስ በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በመገለጡ መሆኑን "ከሥጋ የተነሣ ስለደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፤ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጐአልና እንደመንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ። እንደሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ፈቃድ ያስባሉና እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ።" (ሮሜ 8፥4-5) ያለው ቃል ያስረዳል።

## 6.8.6 የድል አድራጊው ተከታዮችም ሦስቱን ጠላቶች ድል መንሣት ይገባናል፤

### ሀ. ሠይጣንንና ሠራዊቱን፤

እኛ ተከታዮቹ በተሠጠን ሥልጣን አጋንንትን በስሙ ድል ልንነሣቸው ልንቃወማቸው ይገባል። (ሉቃ 10፥17-20, ያዕ 4፥7-8) የመንፈስ የጦር ዕቃዎችንን ልናነሳባቸው (ኤፌ 6፥10-18) ያለምንም ፍርሃት ልንመታቸው ይገባል። ሊውጡን ስለሚፈልጉ ልንነቃባቸው ይገባል (1ጴጥ 5፥8-11) የድል አድራጊው መሢሕ ተከታዮች የሆንን እኛም በዓለም ላይ ያሉ ማኅበረ አጋንንት በእኛም ሆነ በመሢሕ ክርስቶስ ላይ ቢነሡ የምንከተለው ጌታ የድል ጌታ የነገሥታት ንጉሥ ስለሆነ ድል እንነሣቸዋለን "ያየሃቸውም አሥሩ ቀንዶች ገና መንግሥትን ያልተቀበሉ አሥር ነገሥታት ናቸው ዳሩ ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት እንደነገሥታት ሥልጣን ይቀበላሉ እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው። ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ። እነዚህ በጉን ይወጋሉ በጉም የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ስለሆነ እነርሱን ድል ይነሣል። ከእርሱም ጋር ያሉ የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም ደግሞ ድል ይነሣሉ።" (ራዕይ 17፥12-14) ብሎ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው



እንደተናገረው በሮሜም "በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።" (ሮሜ 8፥37) እንደተባለ። እንግዲያውስ ሁላችንም ከሐዋርያው ጋር "ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን" እንበል (1ቆሮ 15፥57)

### ለ. ዓለምንና ክፉውን ምኞት፤

ዓለምን የሚያሸንፈው የእግዚአብሔር ልጅነታችን እምነታችን መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው፤ ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው?" በማለት ይገልጽልናል (1ዮሐ 5፥4-5) ስለክፉው ምኞትም "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን።" ይላል (1ዮሐ 5፥18) ዓለምን የሚወድ ዓለማዊን ሁሉ በተመለከተ ደግሞ "ዓለምን ወይም በዓለም ላይ ያሉትን አትውደዱ በዓ ለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል።" ተብሎ ተጽፏል (1ዮሐ 2፥15-17) እኛ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ብቻ ልንመካ ይገባናል (ገላ 6፥14)

አንባቢ ሆይ ዓለሙ አሸንፎሃል ወይስ አሸንፈኸዋል? ዓለሙ እያስተማረህ ነው ወይስ ዓለሙን እያስተማርከው ነው? ዓለሙ የራሱን ምልክት በአንተ አስቀምጧል? ወይስ አንተ የወንጌልን ምልክት በዓለሙ አስቀምጠሃል?

## ሐ. ሥጋን ድል መንሣት፤

የሥጋ ሥራ ምን እንደሆነ ሥጋ የመንፈስ ጠላት መንፈስ ቅዱስም የእኛን ሥጋ በበጎ ለማሸነፍ በሥጋ ላይ እንደሚነሣና በሕይወታችን የጦር ሜዳነት ሥጋ ድል ከነሣ ምን እንደምናፈራ መንፈስ ድል ከነሣ ምን እንደምናፈራ ቅ/ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ የሚከተለውን ጽፏል። "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛሉና እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ ስለዚህ የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖት ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት ይህን የሚመስል ነው አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሠላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው እንደዚህ ያሉትን ሕግ የሚከለክል ሕግ የለም።" (ገላ 5፥17-23)

አንባቢ ሆይ በአንተ ሕይወት ማን አሸንፎአል? ሥጋ ወይስ መንፈስ ቅዱስ ምን ዓይነት ፍሬስ በሕይወትህ አፍርተሃል? ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት . . . ወይስ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላምን? በሕይወትህ መንፈስ ቅዱስ እንዲያሸንፍ ከፈቀድክ ነጻነትህን ለእሱ አስገዛ ሥጋህን ግን "የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር ሰቀሉ።" (ገላ 5፥24) ተብሎ እንደተጻፈ አንተም ስቀለው በጥምቀት የሥጋን ሥራ ላትሠራ ሞተሃልና ከክርስቶስ ጋርም ተቀብረሃልና እንዲሁም ከእርሱ ጋር ተነሥተህ በክብር ተቀምጠሃልና፤ የሞተ ሰው ኃጢአት ይሠራል? ከመቃብር ወጥተው የሥጋን ፈቃድ ሲያራምዱስ ያየሃቸው አሉን? ይቅርታ አድርግልኝና ከእኔና ከአንተ በቀር? ከክርስቶስ ጋርም በክብር ተቀምጠሃል፤ ታዲያ ምነው ዛሬ በትቢያ ላይ መቀመጥ



ፈቀድክ? "ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንድተሰቀለ እናውቃለን የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቆአልና፤ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን። ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደፊት እንደማይሞት ሞትም ወደፊት እንደማይገዛው እናውቃለንና ... እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታችሁ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ።" (ሮሜ 6፥5-11) ተብሎ የተጻፈውን ተገንዘብ።

## 6.9 ኢየሱስ ክርስቶስ መመኪያችን ነው፤

ሰዎች ሁሉ ከክርስቶስ ውጪ በሌላ ነገር ሊመኩ አይገባም።

### 6.9.1 በሀብታቸው ሊመኩ አይገባም ኃላፊ ጠፊ ነውና፤

1ዜና 29፥12-17, ማቴ 6፥26, ሉቃ 12፥121

### 6.9.2 በኃይላቸው ሊመኩ አይገባም በሕማም በሞት ይለወጣልና፤

1ሳሙ 17፥4-11, 41፥45, መዝ 51፥1-3, ዘካ 4፥6, 2ቆሮ 12፥7-11

### 6.9.3 ሰው በሰው ሊመካ አይገባም ሟች ነውና ሞት ይለውጠዋልና፤

መዝ 117፥8-9, መዝ 145፥3, 1ቆሮ 3፥21-23, 2ቆሮ 10፥13-18

6.9.4 በእውቀት መመካት አይገባም እውቀታችን ከንቱ ነውና፤

1ቆሮ 1፥19-22, 26፥31, 1ቆሮ 8፥2-3

6.9.5 ነገ በሚሆነው መመካት አይገባም ነገን አናውቀውምና፤

ምሳሌ 27፥1, ማቴ 6፥34, ያዕ 4፥13-17

6.9.6 በሥጋችን ወይም በራሳችን መመካት አይገባም፤

ሉቃ 17፥10, ሉቃ 18፥11-14, ኤፌ 2፥9

6.9.7 በብሔር ወይም በዘር መመካት አይገባም፤

ማቴ 3፥9, ሉቃ 3፥8, ዮሐ 8፥33-39, ሮሜ 10፥12, ገላ 3፥28, ቈላ 3፥11, ፊልጵ 3፥3-9, ራዕ 5፥10, ራዕ 7፥9

## በማን እንመካ?

6.9.8 በኢየሱስ ክርስቶስ እንመካ እርሱን የሚልቀው የለምና፤

ሮሜ 5፥11, ሮሜ 15፥17, 2ቆሮ 1፥12, ፊልጵ 3፥3-9

6.9.9 በመስቀሉ እንመካ፤

"ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።" (ገላ 6፥14) በእርሱ የሚመካ "በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው። በውኃ አጠገብ እንደተተከለ በወንዝም ዳር ሥሩን እንደሚዘረጋ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ



ቅጠሉም እንደሚለመልም በድርቅ ዓመትም እንደማይሠጋ ፍሬውንም እንደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል።" (ኤር 17፥7-8)

## 6.10 ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛችን ነው፤

ቤዛ ማለት ለአንድ የተነጠቀ ወይም የተወሰደ ነገር የሚከፈል ዋጋ ወይንም ለውጥ ማለት ነው።

ቤዛ በብሉይ ኪዳን፦ አንድ እስራኤላዊ መሬቱን በድህነት ምክንያት ቢሸጥ የሆነ ሰው መሬቱን በገንዘብ ሊቤዥለት ይችል ነበር (ዘሌ 25፥24-28) እንዲሁም ከተማ ውስጥ የሠራውን ጥሩ ግቢ ያለውን ቤቱን በችግር ምክንያት ቢሸጥ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ማስመለስ ቢችል እጁ ከረጠበ በራሱ ገንዘብ ከሌለው በዘመድ ቤቱን መቤዥት ይችል ነበር (ዘሌ 25፥29-32) እንደዚሁ አንድ ሰው በችግር ራሱን ለሌላው ሰው ባሪያ አድርጎ ለመኖር ራሱን በገንዘብ ቢሸጥ አንደኛ በገንዘቡ ሊቤገው (ነጻ ሊያወጣው) የሚችል ዘመድ ወይንም ወዳጅ ቢያገኝ በገንዘቡ ሊዋጀው ይችል ነበር። ሁለተኛ ገንዘብ ካጠራቀመ የራሱን ነጻነት ባጠራቀመው ገንዘብ ሊቤዥ ይችል ነበር (ዘሌ 25፥39-55, 27፥16-33)

ከዚህ በላይ በከፊል እንደተመለከትነው ቤዛ ማለት አንድን የራስ ሆኖ ኖሮ በኋላ በአንድ ችግር ምክንያት ለሌላ የሆነውን አንድን ነገር መልሶ በገንዘብ ገዝቶ የራስ ማድረግ ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላካችን በብሉይ ኪዳን የሚንገላቱትን፣ የሚቸገሩትን፣ የሚሰቃዩትን ሁሉ ካለባቸው ችግር፣ ሥቃይ በምሕረቱ ይቤገቸው ስለነበር የሕዝብ ቤዛ እንደሆነ የሚከተሉትን ጥቅሶች ልብ እንበል (መዝ 30፥5, 33፥22, 48፥15, ኢሳ 51፥11, ኢሳ 52፥3)

ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘር ሁሉ ቤዛ ነው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚገልጽልን የሰውን ልጅ እግዚአብሔር በመልኩና በአምሳሉ ለራሱ

ክብር ፈጥሮ በተድላ ገነት አስቀምጦት ሳለ ዲያብሎስ ሰውን በኃጢአት ለውጦ በበደል አበላሽቶ የላሜ ልጅ የአውሬዎ ውላጅ ብሎ ገዝቶት ነበር ሰው ራሱን ነጻ ማውጣት ራሱን መቤዠት ስላልቻለ ነጻነቱን አጥቶ ይኖር ነበር። ስለዚህ ራሱን ስለእኛ አሳልፎ በመስጠት ከዲያብሎስ መንግሥትና ከሰይጣናዊ አሠራሩ ነጻ ሊያወጣው ክርስቶስ ወደ ክፉው ዓለም መጣ ይህን በተመለከተ ቅዱስ መጽሐፍ የሚከተለውን ይናገራል። "እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።" ይላል ቤዛ ምዕመናን ክርስቶስ (ማቴ 20፥28) ቤዛነቱም በብዙ መልኩ ነው። በብዙ በኩል ተሸጠን ተለውጠን ነበርና።

### 6.10.1 ስለእኛ ኃጢአተኛ በመባሉ እኛ ጻድቃን ተብለናል፤

"እስመ ዘኢየአምር ኃጢአተ ረሰዮ ኃጥአ በእንቲአነ ከመ ኪያነ ያጽድቀነ ለእግዚአብሔር - ኃጢአት የሌለበት እርሱ ስለእኛ ራሱን ኃጥእ አሰኝቷልና የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን እኛን ጻድቃን ያሰኘን ዘንድ" እንዳለ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ 2ቆሮ 5፥21

### 6.10.2 ስለእኛ መተላለፍ በመቁሰል ከቁስለ ሥጋ ከቁስለ ነፍስ ስለእኛ በደል በመድቀቅ ከድቀተ ሥጋ ከድቀተ ነፍስ ያድነን ዘንድ የበደላችንን ተግሣጽ በመቀበል ተቤዥን የእርሱ አደረገን፤

"እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቈሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፣ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደበጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ



መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።" ተብሎ ተጽፏል (ኢሳ 53፥5-6)

### 6.10.3 ስለእኛ እንደ አንድ ርጉም በእንጨት በመሰቀል ከእርግማን ተቤዠን፤

"በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለእኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤ የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደአሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።" (ገላ 3፥13-14) በመሆኑም "ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ" (ማቴ 25፥34) በክርስቶስ ርግማን (ስለእኛ መረገም) ተባርከናልና እናመስግነው። ቡሩካን ለመባል የበቃነው በመድኃኒታችን ነውና።

### 6.10.4 ስለእኛ መከራን በመቀበል ከመከራ ተቤዠን፤

"የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀብሎአልና" ተብሎ ተጽፎአል (1ጴጥ 2፥21)

### 6.10.5 በደሙ ፈሳሽነት ከበደላችን ተቤዠን፤ (የበደላችንን ሥርየት ሰጠን)

"በውድ ልጅም እንደጸጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ሥርየት ነው" (ኤፌ 1፥7)

### 6.10.6 ስለእኛ በመሞቱ ከሞተ ሥጋ ከሞተ ነፍስ ተቤዠን፤

ቅ/ጳውሎስ በመልእክቱ "ይህን ስለቈረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ።" (2ቆሮ 5፥14) ይላል።

እንዲሁም በ15ኛው ምዕራፍ "እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፦ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለኃጢአታችን ሞተ ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ።" (1ቆሮ 15፥3) በማለት ይናገራል።

በሮሜ መልእክቱም "ነገር ግን ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" (ሮሜ 5፥8) የተባለውን መለኮታዊ ቃል ልብ እንበል።

ቅዱስ ኤፍሬምም "ዘዚአነ ሞተ ነሥአ ወእንቲአሁ ሕይወተ ወሀበነ - የእኛን ሞት ሞቶ የእርሱን ሕይወት ሰጠን" ብሎ የተናገረውንም ልብ እንበል፤

ስለዚህ ቤተክርስቲያንን በከበረ ደሙ ፈሳሽነት ክርስቶስ ስለዋጃት ወይም ስለተቤዠት ለማንም ልትሆን አይገባም። በከበረ ደሙ ተዋጅታለችና "ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፣ ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደበግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።" (1ጴጥ.1፥18-19)

"ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ" (1ቆሮ 6፥19-20) "በዋጋ ተገዝታችኋል የሰው ባሪያዎች አትሁኑ"



(1ቆሮ 7፥23) አዎን ክርስቲያኖች በክቡር በክርስቶስ ደም የተገዛን ነንና በከንቱ ሥራ እንዳንጠመድ ያሻል።

ክርስቲያን ሆይ ዛሬ አንተስ የማን ነህ? በደሙ የገዛህ የጌታህ የኢየሱስ ክርስቶስ ነህን? ወይስ የዓለም? ክርስቶስ በደሙ የገዛውን አንተነትህን አካልህን የዘማ አካል አድርገሸዋልን? ወይስ በክርስቶስ አካል ትሰክር፣ ታመነዝር፣ ትሰርቅ፣ ትገድልበታለህን? በል አንተ የአንተ አይደለህምና በክርስቶስ ቤዛነት ከገሃነመ እሳት የተረፍክ ትንታግ ነህና ንብረትነትህም የክርስቶስ ነውና ማንም እንደጠፍ ከብት አይንዳህ፤ ደሙን ያፈሰሰልህ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለህና ከእርሱ ፊት አትጥፋ።

### 6.10.7 ነፍሱን ስለእኛ አሳልፎ በመስጠት የእኛን ነፍስ ተቤዠልን፤

ማቴ 20፥28, ማር 10፥45, ማር 15፥37, ሉቃ 23፥46, ዮሐ 10፥11-18, ዮሐ 15፥13, ዮሐ 19፥19-30, ኤፌ 5፥2-26, 1ዮሐ 3፥16

## 6.11 ኢየሱስ ክርስቶስ አባታችን ነው፤

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሕዝቡ አምላክ መሆኑን ቀድሞ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ለሕዝቡ አባት ይባል እንደነበረ ያስገነዝበናል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

"አሁን ግን አቤቱ አንተ አባታችን ነህ እኛ ጭቃ ነን አንተም ሠሪያችን ነህ እኛም ሁላችን የእጅህ ሥራ ነን" (ኢሳ 64፥8)

"አብርሃም ባያውቀን እስራኤልም ባይገነዘበን አንተ አባታችን ነህ አቤቱ አንተ አባታችን ነህ ስምህም ከዘለዓለም ታዳጊያችን ነው" (ኢሳ 63፥16)

"ሕጻን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ፣ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘለዓለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።" (ኢሳ 9፥6) ተብሎ እንደተጻፈ ከብሉይ ኪዳን መገንዘብ ይቻላል።

## እግዚአብሔር ለምን የሰው ልጆች ሁሉ አባት ተባለ?

ሀ. እናት የወለደችውን ልጇን እንደምታጽናና ሕዝቡን በነገር ሁሉ ስለሚያጽናና ነው፤ "እናት ልጅዋን እንደምታጽናና እንዲሁ አጽናናችኋለሁ።" (ኢሳ 66፥13)

ለ. አባት ለልጁ እንደሚራራ ይራራልናልና ርኅራኄውን ለመግለጽ "አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል" (መዝ 102፥13)

ሐ. በተፈጥሮ አባታችን ስለሆነ ማለት ፈጣሪያችን ስለሆነ፤ "ደንቆሮ ብልሃተኛም ያልሆንህ ሕዝብ ሆይ ለእግዚአብሔር ይህንን ትመልሳለህን? የገዛህ አባትህ አይደለምን? የፈጠረህና ያጸናህ እርሱ ነው።" (ዘዳግ 32፥7)

መ. እናት እንኳን የወለደችውን ልጇን ብትዘነጋ ሊዘነጋን ስለማይችል፤ "በውኑ ሴት በማኅጸኗ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? አዎን፣ እርስዋ ትረሳ ይሆናል፣ እኔ ግን አልረሳሽም" (ኢሳ 49፥15)

## ኢየሱስ ክርስቶስ አባታችን ነው።

ስንጸልይ አባታችን ሆይ ብለን በልጅነት መንፈስ እንድንጸልይ አዘዘን (ማቴ 6፥8-10) የሁለቱ ልጆች ምሣሌም የእርሱን የአባትነት ምክር አደናቁረው የተቀበሉና በቅን መንፈስ ተቀብለው ያደናቆሩ ምሣሌ ሲሆን



አባትየው ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሣሌ ነው። (ማቴ 21፥28-30) ክርስቲያን ወንድሜ ሆይ አንተስ የአባትህን ቃል ተቀብለህ ተግባራዊ አድርገኸዋልን? ወይስ እሺ ብለህ ቀርተሃል? "እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ እንቢ ብትሉ ግን ብታምጹም ሰይፍ ይበላችኋል የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።" (ኢሳ 1፥9) የተባለውን ልብ በልና ታዘዘው።

የጠፋው ልጅ ምሳሌም እንዲሁ በኃጢአት የባዘነው ዓለም ምሣሌ ሲሆን፣ ትቶት የኮበለለው አባቱ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሣሌ ነበር።

አንተስ ዕድል ፈንታህን ከአባትህ ተካፍለህ (ነጻ ፈቃድህን ተጠቅመህ) ከማን ጋር ትኖራለህ? ከዘማዎች፣ ከሌቦች፣ ከሰካራሞች ጋር ነው ያለኸው? ኧረ ወደ ሩኅሩኅ አባትህ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመለስ።

በተጨማሪ ማቴ 7፥7-12, ሉቃ 11፥3-13, ሉቃ 15፥11-32, ዮሐ 14፥8 ተመልከቱ።

መቼ ተወለድን?

1. ስናምን ገላ 3፥25-29
2. ስንጠመቅ ዮሐ 3፥3-7

ከምን ተወለድን?

- ከማይጠፋው ዘር 1ጴጥ 1፥23-25
- ከውሃና ከመንፈስ ዮሐ 3፥3-4

## የልጅነት መብታችን

- *የልጅነት መብት አለን፤*

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" (ዮሐ 1፥12)

- አባ አባት ብለን የምንጠራበትን መንፈስ ሰጠን፤

“ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮህ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።”

- የአባታችንን መንግሥት እንወርሳለን፤

“ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም ልጅም ከሆንክ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ” (ገላ 4፥7)

## ልጆች ከሆንን፦

### 6.11.1 ለመቀጣት መታገስ ያስፈልገናል፤

“እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር ልጄ ሆይ የጌታን ቅጣት አታቅልል በሚገስጽህም ጊዜ አትድከም ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል፤ ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል ለመቀጣት ታገሱ፤ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸውም ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን? እነርሱ መልካም ሆኖ እንደታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፤ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።” (ዕብ 12፥5-11)



### 6.11.2 ከኃጢአት መራቅ ያስፈልጋል፤

“ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም ዘሩ በእርሱ ይኖራልና ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።” (1ዮሐ 3፥9-10)

### 6.11.3 ልጆች በአባታቸው ፊት በፍቅር እንዲመላለሱ በፍቅር መመላለስ፤

“እንግዲህ እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ ክርስቶስም ደግሞ እንደወደዳችሁ ለእግዚአብሔር የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለእናንተ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።” (ኤፌ 5፥1-2)

### 6.11.4 አባታችንን ማክበር፤

“እናንተ ስሜን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ፣ ልጅ አባቱን፣ ባሪያም ጌታውን ያከብራል እኔስ አባት ከሆንሁ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ ወዴት አለ? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።” (ሚል 1፥6)

### 6.11.5 በብርሃን መመላለስ፤

“የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃን እመኑ አላቸው።” (ዮሐ 12፥36)

### 6.11.6 *አባታችን በፍቅርና በርኅራኄ ፍጹም እንደሆነ አባትን በፍጹምነት መምሰል፤*

"እንግዲህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።" (ማቴ 5፥38)

### 6.11.7 *ርኅሩኅ አባትን መምሰል፤*

"ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ መልካም አድርጉ ምንም ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ ዋጋችሁም ታላቅ ይሆናል የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ እርሱ ለማያመሰግኑ ለክፉዎችም ቸር ነውና አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ ርኅሩኆች ሁኑ።" (ሉቃ 6፥35-36)

### 6.11.8 *አባትን ዘወትር ማመስገን የምስጋና ሰው መሆን፤*

"ሁል ጊዜ ስለሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።" (ኤፌ 5፥20)

## *ልብ ልንለው የሚገባ ዐቢይ ምሥጢር*

በዚህ ልጅነታችን ልብ ልንለው የሚገባ ዓቢይ ምሥጢር ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ እንዲሁም ነን።" (1ዮሐ 3፥1) አዎን የእግዚአብሔር ፍቅር ትልቅና ለእኛ ያለው ትሕትናውም ልዩ ነው፤ እኛ ኃጢአተኞቹን ልጆቹ ላደረገን ክብርና ውዳሴ ዝማሬም ይሁን። አሜን።



## ኢየሱስ ክርስቶስ የክርስቲያኖች ሀብት ነው።

"እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደመቅደስ ሊገቡ እንዳላቸው ባየ ጊዜ ምጽዋትን ለመናቸው ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ትኩር ብሎ ወደ እርሱ ተመልክቶ ወደ እኛ ተመልከት አለው፤ እርሱም አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ ወደ እነርሱ ተመለከተ ጴጥሮስ ግን ብርና ወርቅ የለኝም ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።" (የሐዋ 3፥3-6) እንደተባለ ለቅዱሳን ሐዋርያት ከክርስቶስ ሌላ ወርቅ ብር የላቸውም። አባ ጊዮርጊስም "ወርቅ ዘተመክዐበ የተሰበሰበ ወርቅ፣ ወመድፍን ዘተረክበ - የተገኘ ዕንቊ፣ ምናን ዘረብሐ - ብዙ ሆኖ የረባ ብር ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ - ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ መዝገብነ ዘኢይረክቦ ሠራቂ ወኢያማስኖ ፃዔ ወቊንቊኄ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ - ብል የማይበላው ነቀዝ የማያበላሸው ሌባ የማይሰርቀው ንብረታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" በማለት ነው የተናገረው።

በእርግጥ የሐዋርያት ተከታይ የሆነች የቤተክርስቲያንም ንብረቷ እርሱ ነው። ታዲያ ድኃ ትምሰል እንጂ ሌሎችን የምታበለጽግ ናት ሐዋርያው "የተቀጣን ስንሆን አንገደልም፣ ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፣ ድኆች ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጋ እናደርጋለን፣ አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።" ብሎ እንደተናገረ (2ኛ ቆሮ 6፥10)

እንባቢ ሆይ አንተስ ይህ መዝገብ አለህን? በል ኢየሱስ ክርስቶስን ገንዘብ አድርግ እንደ አባታችን እንደ አባ ኤዎስጣቴዎስ አንድ ቀን ባህር ለመሻገር ፈልገው አንድን መርከበኛ እባክህ እኔንም ደቀመዛሙርቴንም አሻግረን አሉት ገንዘብ ይክፈሉኝ አላቸው እኔ የክርስቶስ ደቀመዝሙር ነኝ ገንዘብ የለኝም አሉት አይሆንም አላቸው እኚህ ታላቅ አባት ክርስቶስን ገንዘብ ያደረጉ፣ ባህርን በሚገስፀው ጌታ

የሚያምኑ ታላቅ አባት ነበሩና “ተወው ሀብቴ ክርስቶስ ውቅያኖሱን ያሻግረኛል” ብለው ከቆዳ የተሠራ አጽፍ ነበራቸው ያን ከውኃው ላይ ዘርግተው ባህሩን ተሻግረው ከተማሪዎቻቸው ጋር ሄዱ ይላል ስለ ሕይወታቸው የሚናገረው የቤ/ክርስቲያን መጽሐፍ። እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን።

<u>ጥያቄዎች</u>

1. ብሉይ ኪዳን መድኃኒት ማንነው ይላል?
2. በሐዲስ ኪዳን ሐዋርያት መድኃኒት ማንነው አሉ?
3. መድኃኒታችን ከዘለዓለማዊ ሞት እንዴት አዳነን?
4. ከኃጢአት እንዴት አዳነን?
5. ኢየሱስ አምላካችን መሆኑን የሚገልጹትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይመልከቱ?
6. ለዘለዓለም የነገሠ ንጉሥ አምላክ መሆኑን በተመለከተ ምን ተመለከቱ?
7. እረኛችን ማን ነው?
8. የበጎቹ ግዴታዎች ምን ምን ናቸው?
9. የእረኛው ግዴታዎች ምን ምን ናቸው?
10. ክርስቶስ ሰላማችን ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?
11. ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌያችን መሆኑን እንብበናል ምሳሌነቱ በምን በምን ነው?
12. ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታችን ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?
13. ሦስቱ ጠላቶቻችን ማን ማን ናቸው?
14. ልንመካባቸው የማይገባቸው ለትምህርት የማይበቁ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
15. ቤዛ ማለት ምን ማለት ነው?
16. ከኃጢአት እንዴት ተቤዠን?



17. ከቁስል ሥጋ እንዴት ተቤዠን?
18. ከርግማን እንዴት ተቤዠን?
19. ከመከራ እንዴት ተቤዠን?
20. ከበደላችን እንዴት ተቤዠን?
21. ከሞት እንዴት ተቤዠን?
22. እግዚአብሔር ለምን የሰው ልጅ ሁሉ አባት ተባለ?
23. የልጅነት መከታችን ምንድን ነው?
24. ልጆች ከሆንን ምን ማድረግ አለብን?
25. ኢየሱስ ክርስቶስ መከታችን ነው ማለት ምን ማለት ነው?

መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
<u>U.S.A.</u>